የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2014 በጀት ዓመት የእቅድ መከታተያ ቼክ-ሊስት

ህዳር 2014

# ማውጫ


1. **መግቢያ** ..... **2**

1.1. የቼክሊስቱ ዓላማ ..... 2

2. **በ2014 በጀት ዓመት የሚከናወኑ አበይት ተግባራት** ..... **3**

3. **የኮሚቴው ዕቅድ ዝርዝር አፈፃፀም** ..... **4**

3.1. የዝግጅት ምዕራፍ (ሕዳር ወር 2014 ዓ/ም) ..... 4

3.2. የተግባር ምዕራፍ (ከታህሳስ ወር 2014 እስከ ግንቦት ወር 2014 ዓ/ም) ..... 5

*3.2.1. በተግባር ምዕራፍ የሚተኮርባቸው ጉዳዮች* ..... *6*

3.3. የማጠቃለያ ምዕራፍ (ሰኔ ወር 2014 ዓ.ም.) ..... 6

4. **የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት** ..... **7**

5. **በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው** ..... **7**

5.1. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ..... 7

5.2. ለሚያጋጥሙ ችግሮች የተቀመጡ መፍትሔዎች ..... 8

6. **የመስክ ምልከታ የሚካሄድባቸው ክልሎችና ርዕሰ ጉዳዮች** ..... **9**

6.1. መደበኛ የመስክ ምልከታ ..... 9

6.2. የቅንጅት የመስክ ምልከታ ..... 11

6.3. የአዲስ አበባ እና ዙሪያው የመስክ ምልከታ ..... 11

7. **የጊዜ ሰሌዳ** ..... **12**

7.1. ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው አስፈፃሚ መ/ቤቶች የአካል ሪፖርት ማቅረቢያ ፕሮግራም ..... 12

7.2. የመስክ ምልከታ ፕሮግራም ..... 13

7.3 ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ ..... 14

## 1. መግቢያ

የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ  በተሻሻለው የም/ቤቱ የአሰራርና የአባላት የሥነ ምግባር ደንብ 6/2008 መሠረት የተለያዩ ኃላፊነቶችና ተግባራት የተሰጡት ሲሆን የግብርና ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት የአመቱን ዕቅድ በብቃት ፈፅመዉ በዘርፉ ዉጤት ተመዝግቦ ምርትና ምርታማነት አድጎ የገጠመን የኢኮኖሚ ቀዉስ ቀንሶ የማየት ራዕይ በመሰነቅ እንዲሁም ቋሚ ኮሚቴዉ ህገ-መንግስታዊ ኃላፊነት በመረዳት ህግ በማዉጣት፣ የክትትልና ቁጥጥር (oversite)፣ ዉክልና እና ድጋፋዊ ክትትል በማድረግ በህዝቡና ምክር ቤቱ የተሰጠዉን ኃላፊነት በብቃት በመወጣት የተጠሪ ተቋማት አፈፃፀም በማሳደግ የህዝቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ተልዕኮ በማንገብ ወደ ሥራ ገብቷዋል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው በግብርናው ዘርፍ፣ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አስተዳደር፣ በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር እንዲሁም ልዩ ድጋፍ በሚሹ ክልሎች ድጋፍ በሚያደርጉ አስፈፃሚ አካላት አሰራሮች ከወጡ የመንግስት ህጎችና የልማት አቅጣጫ አንፃር በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች የአርሶና የአርብቶ አደሩን ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ስራ እየሰሩ ስለመሆናቸው በሁለት ንዑሳን ኮሚቴዎችን በማደራጀት የክትትል፤ ቁጥጥርና ድጋፍ ስራዎችን ይሰራል፡፡

በመሆኑም የ2013 በጀት ዓመት አፈጻጸም እና የም/ቤቱን እና የኮሚቴውን የ2014 ዕቅድ መነሻ በማድረግ በአገራችን የተከሰተውን የኮቪድ-19 ወረርሽኝን መከላከልን እና በአንዳንድ አካባቢዎች በተከሰተው የፀጥታ ችግሮች ከግምት በማስገባት ቋሚ ኮሚቴው በህገ-መንግስቱ በተሰጡት ሥልጣንና ኃላፊነት መሰረት በክትትልና ቁጥጥር የሚከናወኑ ተግባራት መካከል የአስፈጻሚ መ/ቤቶች የዕቅድ አፈጻጸም የአካል ግምገማ፣ የመሰክ ጉብኝት እና የምክክር መድረኮች ተግባራትን ዝርዝር እና የጊዜ ሰሌዳ የሚያሳይ የ2014 በጀት አመት የእቅድ አፈፃፀም መከታተያ ቼክ-ሊስት እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

### 1.1. የቼክሊስቱ ዓላማ

የቋሚ ኮሚቴውን የክትትልና ቁጥጥር ተግባሮቻችን፣ የህግ ማውጣትና የህዝብ ውክልና ተልዕኮዎቹንና ተግባራትን ለማሳካት በአመቱ ውስጥ በተቀናጀና በተናበበ መንገድ በመፈፀም ውጤታማና የአርሶ/አርብቶ አደሩን የላቀ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እውን ለማድረግ እንዲሁም ተጠያቂነትን ማረጋገጥ የሚያስችል ክትትልና ቁጥጥር ሥራዎችን

በማጠናከር በየአስፈጻሚ ተቋማት የተያዙትን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ስኬት መሰረት በመጣል የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነው፡፡

## 2. በ2014 በጀት ዓመት የሚከናወኑ አበይት ተግባራት

ቋሚ ኮሚቴው በ2014 በጀት ዓመት የሚያከናውናቸው አበይት ተግባራት ከዚህ በታች በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡

1) የቋሚ ኮሚቴውን 2014 ዕቅድና የዕቅድ መከታተያ ቼክሊስት በማዘጋጀትና በአባላት ተሳትፎ በማፅደቅ ለም/ቤቱ ማቅረብ፣
2) ለቋሚ ኮሚቴው ተጠሪ የሆኑ የአስፈፃሚ መ/ቤቶችን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ በመገምገም ግብረ-መልስ መስጠት እና በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት ዕቅዱ መከለሱን ማረጋገጥ፣
3) የአስፈፃሚ መ/ቤቶችን ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በየሩብ አመቱ በመገምገም ግብረ-መልስ መስጠት፣
4) ለቋሚ ኮሚቴያችን የሚመሩ ረቂቅ አዋጆችን በመመርመርና በማዳበር የውሳኔ ሀሳብ በማዘጋጀት በወቅቱ ለም/ቤቱ ማቅረብ፣
5) ለቋሚ ኮሚቴው ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ መ/ቤቶች ዙሪያ ከፌዴራል ዋና ኦዲተር የቀረቡ የኦዲት ግኝቶችን አፈጻፀም መገምገም፣
6) የመስክ ምልከታ በማድረግ የአስፈጻሚ አካላት አፈጻጸም ከሪፖርት ጋር የሚጣጣሙና የአርሶ/አርብቶ አደሩን ተጠቃሚነት ያረጋገጡ መሆኑን ማረጋገጥ፣
7) ወሳኝ በሆኑና የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በሚጠይቁ አገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፣
8) የሕዝብ ጥቆማዎችንና አቤቱታዎችን በመቀበል በሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ ማስቻል፣
9) ለቋሚ ኮሚቴው ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ መ/ቤቶች የሴክተር ዘለል ስራዎችን በእቅዳቸው ውስጥ አካትተው እየሰሩ መሆኑን መከታተልና ማረጋገጥ፣
10) የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች በዕቅድና በአፈፃፀም ሪፖርት ተገቢውን ትኩረት አግኝተው ተካትተው መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣

11) የህዝብ ውክልና ስራን ከአባላት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መነሻ በማድረግ መተግበር፣

12) ግብርና ሚኒስቴር እና የግብርና ሚኒስትር ተጠሪ ተቋማት የራሳቸውንና የተጠሪ ተቋማትን የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በአካል ለም/ቤቱ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣

13) የቋሚ ኮሚቴውን የየወሩን፣ የግማሽ ዓመቱንና የዓመቱን ማጠቃለያ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት በማዘጋጀት በም/ቤቱ ለሚመለከታቸው አካላት መላክ፣

14) ከም/ቤቱ የሚመጡ ተጨማሪ ተግባራትንና በቅንጅት መተግበር የሚገባቸውን ተግባራት ማከናወን፡፡

## 3. የኮሚቴው ዕቅድ ዝርዝር አፈፃፀም

ቋሚ ኮሚቴው የዓመቱን ስራዎች በተያዘላቸው ዕቅድ መሰረት ለመፈጸም በሚያስችል ሁኔታ ቼክሊስቱን ያዘጋጀን ሲሆን በሚከታተላቸው ሴክተር መ/ቤቶችም በኩል በተመሳሳይ የአመቱን ዕቅድ ማዕከል በማድረግ ተግባራትን መፈጸማቸውንና ውጤት ማምጣታቸውን መከታተልና መቆጣጠር እንዲያስችል በሶስቱ ምዕራፎች የሚኖሩ ስራዎች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 3.1. የዝግጅት ምዕራፍ (ሕዳር ወር 2014 ዓ/ም)

- የቋሚ ኮሚቴውን የ2014 ዕቅድና የዕቅድ መከታተያ ቼክ ሊስት በማዘጋጀትና በአባላት ተሳትፎ በማፅደቅ ለም/ቤቱ ማቅረብ፣
- የሁለቱን ንዑሳን ኮሚቴዎች ዕቅድ ማዘጋጀትና የጋራ በማድረግ ለኮሚቴው ማቅረብ፣
- የአስፈፃሚ መ/ቤቶችን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ በመገምገም ግብረ-መልስ መስጠትና በተሰጠው ግብረ መልስ መሰረት እቅድ ከልሰው መላካቸውን ማረጋገጥ፣
- መስክ ምልከታዎችን በተመለከተ በየምዕራፉ የቼክ ሊስት ዝግጅት የሚኖር ሲሆን ጊዜውን፣ ቦታውንና የትኩረት መስኮችን ከወዲሁ የመለየት ስራ መስራት፡፡
- አገራዊ የምክክር መድረክ በሚደረግበት አጀንዳ ዙሪያ ከሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች ጋር ስለመድረኩ አስፈላጊነት መግባባት በመፍጠር ለውይይቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ማሰባሰብ መጀመር፣

### 3.2. የተግባር ምዕራፍ (ከታህሳስ ወር 2014 እስከ ግንቦት ወር 2014 ዓ/ም)

በዚህ ምዕራፍ የሚኖሩንን ተግባራት በተመለከተ፡-

- የሴክተር መ/ቤቶችን የአፈፃፀም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ በመቀበል መገምገም፣
- በተመረጠ ሁኔታ በአካል ውይይት ማድረግና የፅሑፍ ግብረ መልስ መስጠት ፣
- እንደየአስፈላጊነቱ በሴክተር መ/ቤቶች የመስክ ምልከታ በማድረግ የተግባራት አፈፃፀም በተደራጀና በተቀናጀ እንዲሁም ወቅታዊ ሁኔታውንና የህዝቡን ፍላጎት ታሳቢ በማድረግ እየተፈጸመ መሆኑን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣
- 10 ዙር መደበኛ፣ 10 ዙር የከተማ፣ ሁለት የቅንጅት እና ሁለት ዙር ድንገተኛ የመስክ ምልከታዎች በማድረግ ለሚመለከታቸውና በየደረጃው ለሚገኙ አካላት የፅሑፍና በየመስክ ምልከታ አካባቢዎች የአካል ግብረ መልስ መስጠት፣ በጣም ወሳኝና አስፈላጊ በሆኑ የመስክ ግኝቶች ላይ በመመስረት ከአስፈጻም መ/ቤቶች ጋር የአካል ውይይት ማካሄድ፣
- ግብርና ሚ/ር የራሱንና የተጠሪ ተቋማትን የአፈፃፀም ሪፖርት በም/ቤቱ በሚፀድቀው ፕሮግራም መሰረት በአካል ለም/ቤቱ እንዲያቀርብ ማድረግ፣
- ቋሚ ኮሚቴው በአሰፈጻሚ መ/ቤቶች የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች፣ የአካል ግምገማዎችና የመስክ ምልከታዎች ያለያቸውን በግብርናው ዘርፍ ማነቆ የሚሆኑ ችግሮች ላይ በተለይ በግብርና ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት እና አጠቃቀም፣ የእንስሳት ዓሳ ሀብት ልማት እና በሽታ ቁጥጥር እንዲሁም በቡና ልማት ገበያና ጥራት ያሉ ማነቆዎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት፣ ከአስፈጻሚው አካላት እና ከህብረተሰቡ ጋር እንደአስፈላጊነቱ በክልሎችም ጭምር እየተገኘ የምክክር መድረኮችን ያካሂዳል፡፡
- ከም/ቤቱ የሚመሩልንን አዋጆች በተገቢው ሁኔታ በመመርመር ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ ለም/ቤቱ በማቅረብ እንዲጸድቁ ማድረግ፣
- የህዝብ ጥቆማዎችንና አስተያየቶችን በመቀበል እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በማሰባሰብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ መስራት፣
- አመታዊ የአርብቶ አደሮች ቀን በዓል ላይ መሳተፍ፤

- ከአቻ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ከም/ቤቱ ጽ/ቤትና ከምንከታተላቸው ሴክተር መ/ቤቶች ጋር በቅንጅት መፈፀም ያለባቸውን ተግባራት በመናበብ መፈፀም፣

### 3.2.1. በተግባር ምዕራፍ የሚተኮርባቸው ጉዳዮች

የሴክተር መ/ቤቶች የየሩብ ዓመት ሪፖርት ከመገምገማችን አስቀድሞ በእያንዳንዱ መ/ቤት ሊተኮርባቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች የመለየት ሥራ የሚሰራ ሲሆን በዚህም መሰረት፡-

- በተግባር አፈፃፀም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ምን እንደነበሩ መገምገም፣
- ሴክተር ዘለል ተግባራት ትኩረት አግኝተውና ውጤት በሚያመጣ መልኩ እየተፈፀሙ ስለመሆናቸው መገምገም፣
- የዋና ኦዲተር የክዋኔና ሂሳብ ኦዲት ግኝትን መሰረት በማድረግ የታዩ ግድፈቶችን ለማረም የሚያስችል ድርጊት መርሃ ግብር ተዘጋጅቶ እየተተገበረ መሆኑን ማረጋገጥ፤
- የበጀት አፈፃፀም ከተግባራት ፊስካል አፈፃፀም ጋር ያላቸውን ቁርኝት እና መናበብ መገምገም፣
- ለምንሠራቸው ተግባራት በሙሉ የተለቀመና የተደራጀ ግብረ መልስ መስጠት እንዲሁም በተሰጠው ግብረ መልስ መሠረት መፈፀሙን መከታተል፣
- በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት ድክመት የታየባቸውን ስራዎችና ከሌሎች ሴክተሮች ጋር በቅንጅት የሚፈፀሙ ተግባራትን በመለየት ዋነኛ ማነቆዎቻቸውን ነቅሶ በማውጣትና መወያያ አጀንዳ በመለየት የውይይት መድረክ በማዘጋጀትና በብቃት በመምራት ውጤታማ ስራ መስራት፡፡

## 3.3. የማጠቃለያ ምዕራፍ (ሰኔ ወር 2014 ዓ.ም.)

በማጠቃለያ ምዕራፍ የሚኖሩን ተግባራት፣

- ሁሉም ተግባራት በደረሱበት ሲጠናቀቁ የማጠቃለያ ግምገማ በማድረግ መዝጋት፡፡
- የንዑስ ኮሚቴዎችንና የቋሚ ኮሚቴውን የ2014 በጀት ዓመት የስራ አፈፃፀም በመገምገም ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በተገቢው መለየት፣

## 4. የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት

ዝርዝር የተግባራት እቅድ ከተቀመጠው ግብና አላማ አኳያ እየሄደ መሆኑን በተቀመጠው የጊዜ ሠሌዳና የተግባራት መከታተያ ቼክሊስት መሰረት ክትትልና ቁጥጥር የምናደርግ ሲሆን፣

**በዋናነት የሚፈፀሙ ተግባራትም:-**

- የቋሚ ኮሚቴው የንዑሳን ኮሚቴ አመራሮች በየሳምንቱ (ረቡዕ ከሰዓት) እየተገናኙ ስራዎች ያሉበትን ደረጃ መገምገምና አቅጣጫ ማስቀመጥ፣
- ሁለቱምም ንዑሳን ኮሚቴዎች በእቅዳቸው መሠረት የሚከታተሏቸውን መ/ቤቶች እቅድና አፈፃፀም እየገመገሙ ግብረ-መልስ ማዘጋጀትና ወደ ጋራ መድረክ መምጣት የሚኖርባቸውን ጉዳዮች ማቅረብ በኮሚቴ ደረጃ መወያየት፣
- በየሩብ አመቱ የሴክተር መ/ቤቶችን ሪፖርት በመገምገም ግብረ-መልስ መስጠት፣
- በአካል በመስክ በመገኘት የመስክ ምልከታ ማድረግ እና ግብረ መልስ መስጠት፣
- በየወሩ በንዑስ ኮሚቴና (ከ28 እስከ 30 ባለው) በአብይ ኮሚቴ (ከ1 እስከ 3 ባለው) ደረጃ የስራ አፈፃፀም መገምገም እንዲሁም በአመት ሁለት ጊዜ /ጥር እና ሰኔ/ በዝርዝር የተግባራት አፈጻጸም ግምገማ በማድረግ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ለም/ቤት አፈ-ጉባኤ፣ ለም/ቤት ጽ/ቤት እንዲሁም ለመንግስት ተጠሪ መላክ፣
- በተለያዩ የስልጠና መድረኮች የተሳተፉ አባላት ለሌሎች ያልሰለጠኑ አባላት በአጭሩ እንዲያስገነዝቡ ፕሮግራም በማውጣት መፈጸም፣

## 5. በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው

### 5.1. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

- ወቅታዊ የአገራችን ችግር የሆኑት የኮቪድ-19 እና የፀጥታ ችግሮች ቋሚ ኮሚቴ በበጀት ዓመቱ ለማከናወን ያያዛቸውን ዕቅዶች ለመተግበር እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ፣
- አንዳንድ አስፈፃሚ መ/ቤቶች እቅድና ሪፖርታቸውን በወቅቱ ጥራቱን ጠብቀውና በአመራር ገምግመው ያለማቅረብ እና በተሰጣቸው ግብረ መልስ መሠረት እጥረቶችን ያለማረም፣

- በም/ቤቱ ደራሽ ሥራዎች፣ በተለያዩ ስልጠናዎችና ስብሰባዎች ምክንያት የቋሚ ኮሚቴያችንን ሥራዎች በተቀመጠው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት መፈጸም ያለመቻል፣
- ለመስክ ምልከታ የተሽከርካሪ፣ የበጀትና የጊዜ እጥረት፣ በቂ የሚዲያ ሽፋን ያለማግኘት ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡
- አልፎ አልፎ አንዳንድ የቋሚ ኮሚቴው አባላት የመቅረት፣ የማርፈድ፣ በጥቃቅን ምክንያቶች ፍቃድ ማብዛትና በጥራት ተልዕኮን አለመወጣት ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ከም/ቤቱ ጽ/ቤትና ከአንዳንድ ድጋፍ ሰጭ ባለሙያዎች ቀልጣፋና ተገቢውን አገልግሎት ማግኘት ያለመቻልና የቅንጅት ችግሮች ሊያጋጥሙን ይችላሉ፡፡
- ለኮሚቴው መሰባሰቢያ አዳራሽ በሌላ ስብሰባ ሲያዝ መቸገር ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል፡፡

## 5.2. ለሚያጋጥሙ ችግሮች የተቀመጡ መፍትሔዎች

- የጤና ሚኒስቴር በሚያስቀምጠው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከላከል መመሪያ መሰረት የሚያስፈልጉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን በመተግበር ማከናወን እንዲሁም የጸጥታ ችግሮች እንዳያጋጥሙ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር መስራት፣
- የአስፈፃሚ መ/ቤቶች እቅድና የአፈፃፀም ሪፖርታቸውን የማቅረቢያ ጊዜ በጋራ በስምምነት በመወሰን ወቅቱን ጠብቀው በተቀመጠው ጊዜ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣
- ስራዎች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲሰሩ ጥረት ማድረግ፣ ጊዜው በአጣዳፊ ሥራዎች በሚያዝበት ጊዜ በሌላ ቀናት እንዲካካስ ማመቻቸት፣
- የሚያስፈልጉ አገልግሎቶች በግልጽ የድርጊት መርሃ ግብር በማስደገፍ አስቀድሞ አገልግሎቱን ለሚሰጡ አካላት እንዲደርሳቸው ማድረግ፣
- የቋሚ ኮሚቴው አባላት ሕዝብና መንግስት የሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ቅድሚያ ለኮሚቴው ሥራ እንዲያደርጉ ማድረግ፣ ችግሩ ሲከሰት በንዑስ ኮሚቴና በሥራ ቡድን ክትትልና ግምገማ ማስተካከል፣
- የአዳራሽ ችግርን ለመሻገር አስቀድሞ ፕሮግራም መኖሩን በማሳወቅ ማስያዝ፤

# 6. የመስክ ምልከታ የሚካሄድባቸው ክልሎችና ርዕሰ ጉዳዮች

## 6.1. መደበኛ የመስክ ምልከታ

### 6.1.1. የብዝሀ ህይወት እና ቡና ልማት ማዕከል በማድረግ የሚደረግ የመስክ ምልከታ

በተመሳሳይ መልኩ ከቋሚ ኮሚቴዎች የተውጣጡ አባላት እና ባለሙያዎች በህዳር ወር 2014 ዓ.ም በደቡብ ምዕራብ ክልል ከፋ እና ዳዉሮ ዞን እና በኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ ዞን ብዝሀ-ህይወት እና ቡና ልማት መሰረት በማድረግ የመስክ ምልከታ የሚከናወን ይሆናል፡፡

### 6.1.2. ኩታ ገጠም እርሻ እና አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ማዕከል በማድረግ የሚደረግ የመስክ ምልከታ

የመጀመሪያ ዙር የመስክ ምልከታ በታህሳስ ወር 2014 ዓ.ም በአሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት አርሲ ዞን የሚካሄደውን የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እንዲሁም የኩታ ገጠም እርሻ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ክልል በጋሞ ዞን አትክልትና ፍራፍሬ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ የመስክ እይታ በማድረግ የመስክ ምልከታ የሚካሄድ ሲሆን ከቋሚ ኮሚቴዉ የተውጣጡ አባላት እና ባለሙያዎች የሚሳተፉበት ይሆናል፡፡

### 6.1.3. የእንስሳት እና አረንጓዴ አሻራ ስራዎችን ማዕከል በማድረግ የሚደረግ የመስክ ምልከታ

የእንስሳት እና አረንጓዴ አሻራ ስራዎችን ማዕከል በማድረግ በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን እና ቤንቺ ሸኮ ዞን የእንስሳት እና አረንጓዴ አሻራ የሥራ እንቅስቃሴ ማዕከል በማድረግ የሚደረግ መስክ ሲሆን ከቋሚ ኮሚቴዎች የተውጣጡ አባላት እና ባለሙያዎች በታህሳስ ወር 2014 ዓ.ም የሚሰማሩ ይሆናል፡፡

### 6.1.4. እንስሳት ሀብት እና የመስኖ ልማትን ማዕከል በማድረግ የሚደረግ የመስክ ምልከታ

በአፋር እና ሱማሌ ክልል የእንስሳት ሀብት እና የመስኖ ልማት ተግባራትን ማዕከል በማድረግ የሚደረግ የመስክ ምልከታ ሲሆን ከቋሚ ኮሚቴ የተውጣጡ አባላት እና ባለሙያዎች በጥር ወር 2014 ዓ.ም የሚሰማሩ ይሆናል፡፡

### 6.1.5. የህብረት ስራ ማህበራት ዉጤታማነት ማዕከል በማድረግ የሚደረግ የመስክ ምልከታ፣

በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን እና በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን የህብረት ስራ ማህበራትን መሰረት በማድረግ የስራዎችን እንቅስቃሴ ማዕከል በማድረግ ከቋሚ ኮሚቴዎች የተውጣጡ አባላት እና ባለሙያዎች መጋቢት ወር 2014 ዓ.ም የሚሰማሩ ይሆናል፡፡

### 6.1.6 የግብርና ኢቨስትመንት ስራዎችን ማዕከል በማድረግ የሚደረግ የመስክ ምልከታ፣

በጋምቤላ እና ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል የግብርና ኢንቨስትመንት ስራዎችን እንቅስቃሴ ማዕከል በማድረግ ከቋሚ ኮሚቴዎች የተውጣጡ አባላት እና ባለሙያዎች መጋቢት ወር 2014 ዓ.ም የሚሰማሩ ይሆናል፡፡

### 6.1.7 የተፈጥሮ ሀብት ስራዎችን ማዕከል በማድረግ የሚደረግ የመስክ ምልከታ፣

በድሬደዋ እና ሀረር ክልል የተፈጥሮ ሀብት ስራዎችን እንቅስቃሴ ማዕከል በማድረግ ከቋሚ ኮሚቴዎች የተውጣጡ አባላት እና ባለሙያዎች ሚያዝያ ወር 2014 ዓ.ም የሚሰማሩ ይሆናል፡፡

### 6.1.8 የምግብ ዋስትና እና ግብርና ፕሮጀክት ስራዎችን ማዕከል በማድረግ የሚደረግ የመስክ ምልከታ፣

በሲዳማ ክልል እና አላባ ዞን የምግብ ዋስትና ስራዎች እና የግብርና ፕሮጀክት ስራዎችን እንቅስቃሴ ማዕከል በማድረግ ከቋሚ ኮሚቴዎች የተውጣጡ አባላት እና ባለሙያዎች ሚያዝያ ወር 2014 ዓ.ም የሚሰማሩ ይሆናል፡፡

### 6.1.9 የበልግ ማጠቃለያ እና የመኸር ዝግጅት ስራዎችን ማዕከል በማድረግ የሚደረግ የመስክ ምልከታ፣

በደቡብ ምዕራብ ክልል በሀድያ ዞን እና በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ አርሲ የበልግ ማጠቃለያ እና የመህር ዝግጅት ስራዎችን እንቅስቃሴ ማዕከል በማድረግ ከቋሚ ኮሚቴዎች የተውጣጡ አባላት እና ባለሙያዎች ግንቦት ወር መጀመሪያ 2014 ዓ.ም የሚሰማሩ ይሆናል፡፡

### 6.1.10 የአርብቶ አደር ስራዎችን ማዕከል በማድረግ የሚደረግ የመስክ ምልከታ፣

በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን እና በደቡብ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን የአርብቶ አደር አካባቢ ነዋሪዎች ተጠቃሚነት ከማድረግ አንጻር የተሰሩ ስራዎችን እንቅስቃሴ ማዕከል በማድረግ ከቋሚ ኮሚቴዎች የተውጣጡ አባላት እና ባለሙያዎች ግንቦት ወር መጀመሪያ 2014 ዓ.ም የሚሰማሩ ይሆናል፡፡

## 6.2. የቅንጅት የመስክ ምልከታ

### 6.2.1. የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ልማት

የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ልማት ስራዎችን ማዕከል በማድረግ በቡልቡላ (ኦሮሚያ ክልል) እና በይርጋለም (ደቡብ ክልል) ከኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር በቅንጅት የመስክ ፕሮግራም እንደሚኖረን ታሳቢ ተደርጎ የተያዘ ሲሆን የቋሚ ኮሚቴያች አባላት እና ባለሙያዎች ቋሚ ኮሚቴዎች የጋራ የሚያወጡት የጊዜ ሰሌዳ የሚከናወን የሚሰማሩ ይሆናል፡፡

### 6.2.2. የመስኖ ልማት ስራዎች በተመለከተ

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከዉሃ መስኖ ቆላማ አካባቢና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጋር በቅንጅት የመስክ ፕሮግራም እንደሚኖረን ታሳቢ ተደርጎ የተያዘ ሲሆን የኮሚቴያችን አባላት እና ባለሙያዎች በቋሚ ኮሚቴዎች የጋራ የሚያወጡት የጊዜ ሰሌዳ የሚከናወን የሚሰማሩ ይሆናል፡፡

## 6.3. የአዲስ አበባ እና ዙሪያው የመስክ ምልከታ

በተመረጡ ሴክተሮችና ርዕስ ጉዳዮች ላይ በማተኮር አስር የከተማ መስክ ምልከታ የምናካሂድ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት የሚከናወኑ የመስክ ምልከታዎች፡-

1) በግብርና ሚስቴር መ/ቤት የሥራ እንቅስቃሴን በአካል ተገኝቶ መገምገም እና ድጋፍ መስጠት፣
2) ሌሎች ለግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተጠሪ የሆኑ ተቋማትን በዋና እና ቅርንጫፍ ያሉ ሥራዎች ያሉበትን ሁኔታ ለመገምገም፣

## 7. የጊዜ ሰሌዳ

### 7.1. ቋሚ ኮሚቴው የሚከታተላቸው አስፈፃሚ መ/ቤቶች የአካል ሪፖርት ማቅረቢያ ፕሮግራም

| ተ.ቁ | ሪፖርት አቅራቢ መ/ቤት | ሪፖርት የሚያቀርቡበት ጊዜ | | | አስፈጻሚ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በዝግጅት ምዕራፍ (ጥቅምት) | በተግባር ምዕራፍ (ከሕዳር -ግንቦት) | በማጠቃለያ ምዕራፍ (ሰኔ) | | |
| 1 | ግብርና ሚኒስቴር | | ታህሳስ 11/2014 | ጥር ወር/2014 | የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ | የ6 ወራት ለኮሚቴ እና የ6 ወራት ለም/ቤት |
| 2 | የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት፣ | | ታህሳስ 20/2014 | | የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ | የ6 ወራት |
| 3 | የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ | | ጥር 02/2014 | | የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ | የ6 ወራት |
| 4 | የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን፣ | | ጥር 18/2014 | | የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ | የ6 ወራት |
| 5 | የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን፣ | | መጋቢት 14/2014 | | የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ | የ6 ወራት |
| 6 | የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን፣ | | መጋቢት 28/2014 | | የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ | የ6 ወራት |
| 7 | የእንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት፣ | | ሚያዚያ 12/2014 | | የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ | የ9 ወራት |
| 8 | የኢትዮጵያ ደን ልማት፣ | | ሚያዚያ 26/2014 | | የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ | የ9 ወራት |
| 9 | የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት፣ | | ግንቦት 08 /2014 | | የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ | የ9 ወራት |
| 10 | የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት | | ግንቦት 17 /2014 | | የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ | የ9 ወራት |

## 7.2. የመስክ ምልከታ ፕሮግራም

| ተ.ቁ | የመስክ ምልከታ የሚካሄድበት ቦታ | የመስክ ምልከታ የሚካሄድበት ጊዜ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ጊዜ | የቆይታ ቀናት | ምርመራ |
| 1 | በደቡብ ምዕራብ ክልል ከፋ እና ዳዉሮ ዞን እና በኦሮሚያ ክልል ቡኑ በደሌ ዞን ብዝሀ-ህይወት እና ቡና ልማት መሰረት በማድረግ | ህዳር 20 - 30/ 2014 ዓ.ም. | 10 | |
| 2 | በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት አርሲ ዞን የሚካሄደውን የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እንዲሁም የኩታ ገጠም እርሻ እና በደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ክልል በጋሞ ዞን አትክልትና ፍራፍሬ የሥራ እንቅስቃሴ | ታህሳስ 01 - 15 /2014 ዓ.ም. | 15 | |
| 3 | በአፋር እና ሱማሌ ክልል የእንስሳት ሀብት እና የመስኖ ልማት ተግባራትን ማዕከል በማድረግ | ታህሳስ 15 - 30/2014 ዓ.ም. | 15 | |
| 4 | የእንስሳት እና አረንጓዴ አሻራ ስራዎችን ማዕከል በማድረግ በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን እና ደቡብ ክልል ቤንቺ ሸኮ ዞን | ጥር 01 - 15 / 2014 ዓ.ም. | 15 | |
| 5 | በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን እና በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን የህብረት ስራ ማህበራትን መሰረት በማድረግ | ጥር 16 - 30/2014 ዓ.ም. | 15 | |
| 6 | በጋምቤላ እና ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል የግብርና ኢንቨስትመንት ስራዎችን እንቅስቃሴ ማዕከል በማድረግ | መጋቢት 01- 15/2014 ዓ.ም | 15 | |
| 7 | በድሬደዋ እና ሀረር ክልል የተፈጥሮ ሀብት ስራዎችን እንቅስቃሴ ማዕከል በማድረግ | መጋቢት 16 - 30/2014 ዓ.ም | 15 | |
| 8 | በሲዳማ ክልል እና አላባ ዞን የምግብ ዋስትና ስራዎች እና የግብርና ፕሮጀክት ስራዎችን እንቅስቃሴ ማዕከል በማድረግ | ሚያዚያ 01 - 15/2014 ዓ.ም | 15 | |
| 9 | በደቡብ ክልል በሀድያ ዞን እና በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ አርሲ የበልግ ማጠቃለያ እና የመኸር ዝግጅት ስራዎችን እንቅስቃሴ ማዕከል በማድረግ | ሚያዚያ 15 - 30/2014 ዓ.ም | 15 | |
| 10 | በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን እና በደቡብ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን የአርብቶ አደር አካባቢ ነዋሪዎች ተጠቃሚነት ከማድረግ አንጻር የተሰሩ ስራዎችን | ግንቦት 01 - 15/2014 ዓ.ም | 15 | |
| 12 | የቅንጅት የመስክ ምልከታው | በቋሚ ኮሚቴዎች የጋራ የሚያወጡት የጊዜ ሰሌዳ የሚከናወን ይሆናል፡፡ | | |
| 13 | የከተማ መስክ ምልከታ | በአስፈላጊው ጊዜ | | |

## 7.3 ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ

| ተ.ቁ. | የምክክሩ ርዕሰ ጉዳይ | የሚደረግበት ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | በቡና ልማት ገበያና ጥራት ያሉ ማነቆዎች | ታህሳስ 08/2013 ዓ.ም. |
| 2 | በግብርና ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት እና አጠቃቀም፣ | ጥር 23/2014 |
| 3 | የእንስሳት ዓሳ ሀብት ልማት እና በሽታ ቁጥጥር | ሚያዚያ 03/2014 |